

# ~ 10 ~

# ሰዱቃዊ (ቆሳቁሳዊ)

10-1

## የሰዱቃውያን እንቅስቃሴ

በክርስቶስ ዘመን ከነበሩት የአይሁድ እንቅስቃሴዎች ወይንም ክፍሎች ሰዱቃውያን አንደኛው ክፍል ነው። ስለፈሪሳውያን የተጻፈውን ያህል ስለእነርሱ የተጻፈ ሰፊ ታሪክ የላቸውም። እንዲያውም መኖራቸው በግልጽ የታወቀው ከባቢሎን ምርኮ በኋላ ሲሆን፥ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ጊዜ እንቅስቃሴያቸው ግልጽ እየሆነ መጣ። ሰዱቃውያን ከፈሪሳውያን እምነትና አቋም ብዙ የሚመሳ ስሉበት ሁኔታዎች ቢኖራቸውም፥ በዚያው ልክ ልዩነታቸውም በጣም ሰፊ ነው። ፈሪሳውያን ግትር የሆኑ ሕግ አጥባቂዎች ሲሆኑ፥ ሰዱቃውያን ደግሞ ከተራው ሕዝብ ጋር የማይቀላቀሉ ከበርቴዎች ወይንም ሀብታሞች ነበሩ። ሰዱቃውያን በጽሁፍ የሠፈረውን ሕግ ብቻ እንጂ የአቦውን ወግ ሥርዓትና ደንብ አይከተሉም። ሕግን በሚመለከት ጉዳይ ጥብቅ ስለሆኑ፥ ማንኛቸውንም የሙሴ ሕግ ተላላ ፊዎች ያለ ይቅርታ ይቀጣሉ። የሙሴን ሕግ ቃል በቃል እንጂ እንደፈሪሳውያን የሕግን ትርጉም አይመለከትም።

## የሰዱቃውያን እምነት

1. ሰዱቃውያን "የሙታን መነሳት የለም" የሚሉ ናቸው (ማቴ. 22፥23)። ሰዱቃውያን በሙሴ ሕግ ውስጥ ያልተጠቀሰውን ማንኛውንም እውነት የሚመስለውን ሀሳብ አይቀበሉም። በሙሴ የሕግ መጽሐፍት ስለሙታን መነሳት በግልጽ የተጻፈ ነገር ስለሌለ ሀሳቡን መቀበል ያቅታቸዋል። ክርስቶስ እነዚህን ሰዱቃውያንን ስለ ሙታን መነሳት ሲያስረዳ እንዲህ አላቸው። "ስለ ሙታን መነሳት የሆነ እንደሆነ ግን እግዚአብሔር ሙሴን በቁጥቋጥ እሳት ውስጥ ምን እንደተናገረው ከሙሴ መጽሐፍ አላነበባችሁም? "እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ" ያለው ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር የህያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም፤ እናንተ ግን እጅግ ትስታላችሁ" (ማር. 12፥26-27)።

2. ሰዱቃውያን "ትንሳኤ የለም፤ መላዕክትም የሉም፤ መንፈስም የለም" ብለው ያምናሉ (የሐዋ. 23፥8)። መንፈስ አይኖርም የሚሉበትን ምክንያት ሲያስረዱ "መንፈስ ከሥጋ ጋር አብሮ ይጠፋል" ይላሉ። ሰዱቃውያን ዋና ትኩረታቸው ጊዜያዊ በሆነው ቆሳቁሳዊ በሆነ ነገር ላይ ነው። ከሞት በኋላ ሌላ ሕይወት አለ ብለው እንዲሁም የኢየሱስን ከሞት መነሳት ጴጥሮስና ዮሐንስ ጠቅሰው በማስተ ማራቸው ሰዱቃውያን ተቆጥተው ከወህኒ ቤት ጣሏቸው (የሐዋ. 4፥1-2)።

## የሰዱቃውያን አቋም

ሰዱቃውያን ከተራው ሕዝብ በጣም የራቁ፣ በአኗኗራቸውና በደረጃቸው በሕብረተሰብ ውስጥ ከፍ ብለው የሚታዩ ነበሩ። ከሚያስፈልጋቸው በላይ የሚሰበስቡና የሚያከማቹ ሲሆን፥ ስለራሳቸው እንጂ የሌላው መራብና መቸገር ወደ ውስጣቸው አይገባም። ሌሎች የተጨቆኑ፣ በብርቱዎች የተበዘበዙ፣ በኢኮኖሚው ውስጥ ድርሻ እንዲኖራቸው የመረዳት ፍላጎትና ጥረት አይታይባቸውም። ጊዜያዊውን ነገር በመሰብሰብ በብርቱ የሚታገሉ፣ ዓይናቸው ደካማውንና የተራበውን እንዳያይ በቁሳቁሳዊ ነገር የሸፈኑ ናቸው። ገንዘባቸው አምላካቸው ከመሆኑም በላይ "በገንዘባችን ኃይል የፈቀድነውን ነገር ማድረግ እንችላለን" ብለው የሚያምኑ ናቸው። ሙከራቸውም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተጽፎ ይገኛል። የክርስቶስን እሬሳ ይጠብቁ ለነበሩት ወታደሮች ገንዘብ በመስጠት "የክርስቶስን ሬሳ ደቀመዛሙርቱ በሌሊት መጥተው ሰርቀው ወሰዱት" ብለው እንዲያወሩ አድርገዋል። በገንዘባቸው ኃይል የክርስቶስ የትንሳኤ ኃይል ተጭበርብሮ እንዲቀር መሞከራቸውን እናያለን።

## የዘመኑ ሰዱቃውያን

ሰዱቃውያን በክርቶስ ዘመን ብቻ የነበሩ ሳይሆን በዘመናችንም አሉ። "ሞትና ትንሳኤ" የለም ብለው ባያምኑም በብዙ አቅጣጫ ሰዱቃውያንን ይመስላሉ። ይኸውም በጊዜያዊ በሆነው ቁሳቁስ ላይ ያተኮሩና ልባቸውን አብዝተው የሰጡ ናቸው። ባሉበት ህብረተሰብ ውስጥ ባላቸው ከፍተኛ አቋም የተነሳ የክርስቶስ ወንጌል እንዳይስፋፋ ከፍተኛ እንቅፋት ይሆናሉ። ሰዱቃውያን ዓለምንና በውስጧ ያለውን መውደድ የሚያመጣውን ችግር የተረዱ አይደሉም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ምድራዊ ብልጽግና፥

1. እርካታ የለውም

   በምድራዊ ነገር ላይ ያተኮረ ሰው እርካታ የለውም። በቃኝን አያውቅም። በአለውም ደስ ብሎት መኖር አይችልም። በብልጽግና ብዛት ደስታን የሚያገኝ ስለሚመስለው መሰብሰቡን አያቆምም። "ብርን የሚወድድ ሰው ብርን አይጠግብም፤ ባለጠግነትንም የሚወድድ ትርፉን አይጠግብም፤ ይህም ደግሞ ከንቱ ነው" ይላል መክ. 5፥10። አማኝ ከዚህ ፈተና መሸሸ አለበት። ሃናንያና ሳፊራ ተሰነካክለው የወደቁት በገንዘብ ምክንያት ነው። ስለዚህ ነው ሃዋርያው ጴጥሮስ "የልቦናችሁን ወገብ ታጥቃችሁ በመጠን ኑሩ" በማለት የሚመክረን (1ጴጥ. 1፥13)። ዮሐንስም ዓለምን እንዳንወድ ጥብቅ የሆነ ማሳሰቢያ ይሰጠናል። "ዓለምን ወይንም በዓለም ያሉትን አትውደዱ፣ በዓለም ያለው ሁሉ እርሱም የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮ ስለ ገንዘብም መመካት ከዓለም ስለሆነ እንጂ ከአባት ስላልሆነ ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም። ዓለሙም ምኞቱም ያልፋል፤ የእግዚአብ ሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘለዓለም ይኖራል (1ኛ. ዮሐ. 2፥15-17)።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። እሜን!**

2. ወጥመድ ነው

   ምድራዊ ሀብት አገልግሎቱ ሰፊ ይሁን እንጂ አደገኛነቱም በዚያው ልክ ነው። "ገንዘብ መውደድ የክፉት ሁሉ ሥር ነውና አንዳንዶችም ይህን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ" ይላል 1ኛ. ጢሞ. 6፥10። ያዕቆብም ይህንኑ ሲያስረድ "ወርቃችሁም ብራችሁም ዝጎአል፤ ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል፤ ሥጋችሁንም እንደ እሳት የበላል" ይላል (ያዕ. 6፥3)። ሥጋዊ ብልጽግናን የሚመኙ ሁሉ ሳይውቁት ጠልፎ ከሚጥላቸው መጥመድ ውስጥ ይገባሉ (1ኛ. ጢሞ. 6፥9-10)።

3. የደህንነትን መንገድ ይዘጋል

   አንድ ቀን አንድ ሀብታም በጉልበቱ ተንበርክኮ "የዘለዓለምን ህይወት እንዳገኝ ምን ላድርግ?" ብሎ

ከልቡ ጠየቀ። ኢየሱስም ሲመልስለት “ያለህን ሽጠህ ተከተለኝ” አለው (ማር. 10፥17-22)። የወጣቱ ልብ ያረፈው በቆሳቁሳዊ ነገር ላይ ስለነበረ ያንን መተው አቃተው። በዚህም ምክንያት ፊቱን አዙሮ እያዘነ በመጣበት ተመለሰ። ከፊቱ የተዘረጋውን የደህንነት መንገድ ረግጦ ፊቱን ወደ ሲኦል መልሶ ሄደ። ይህ ወጣት በጊዜያዊ ነገር በመሳብ የዘለዓለምን ህይወት አጣ። ሰዱቃውያን ልባቸው ያረፈው ቆሳቁሳዊ በሆነ ነገር ላይ እንደነበረው፥ በዘመናችንም ልባቸውን በገንዘብ ላይ ያሳረፉ ብዙዎች ናቸው። **“ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ፥ ነፍሱን ግን ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?”** ያለው በማርቆስ 8፥36 ላይ፥ በምድራዊ (ቆሳቁሳዊ) ነገር ላይ የታሠሩትን ሰዎች ሲጠቅስ ነው።

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**